www.ginbot7.org

# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7፣ የፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

ሃሙስ ሐምሌ 17 2000 ዓም ቁጥር 10

---

## ታጣቂዎች በተቀናጀ እቅድ አራት ሥፍራዎችን ተቆጣጠሩ፡፡

## "ሲለበለብ፣ እንኳን ሰው ወተትም ይገነፍላል" የግንቦት7 አመራር

ሰኔ 29 2000 ዓ.ም ከእኩለ ሌሊት አንስቶ አስከ ሌሊቱ 10 ሰዓት ድረስ፣ የዓለም ከተማ፣ ታች ቤት ወረዳ ፌጠራ፣ መራኛና ኦሮሞ ዋጂ ቱሬ የተባሉ የሰሜን ሸዋ ስፍራዎች  የመለስ ዜናዊን ግፈኛ አገዛዝ በሚቃወሙ ሃይሎች እጅ ወድቀው እንደነበር ተረጋገጠ።  ታጣቂዎቹ በአራቱም ስፍራዎች በአንድ ጊዜና በተመሳሳይ ሰአት በመግባት ስፍራውን ለመቆጣጠር እንደቻሉና በዚህም ጊዜ ባካባቢው ከነበሩ የፖሊስ ሃይሎችና ሚሊሻዎች ምንም ዓይነት ተቃውሞ እንዳልገጠማቸው የግንቦት 7 አስተማማኝ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ራሳቸውን "የአንድነት ሃይሎች" በማለት ለህዝብ ያስተዋወቁት እነዚሁ ታጣቂዎች፤ ሜጋፎን በመጠቀም ለአካባቢው ህዝብ ስለድርጅታቸው ዓላማ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡እንደ፡ግንቦት፡7 አስተማማኝ መረጃዎች፡ከሆነ፡ ታጣቂዎቹ ባደረጉት ቅስቀሳ፤ የሚንቀሳቀሱበት ዓለማ በህዝብ ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ላለማድረስ አልሞ የተነሳ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እስካሁን በአከባቢው የወያኔ ኢህአዴግ መሳሪያዎችና አገልጋዮች የነበሩ ግለሰቦችም ከእንግዲህ ወያኔ ኢህአዴግን በመተው እና ህዝቡንና የአንድነት ሃይሎችን  በመቀላቀል የበደሉትን ህዝብ መካስ እንደሚገባቸው ያስገነቡት እነዚሁ ታጣቂዎች፤ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኞች እስከሆኑ ድረስ የአንድነት ሃይሎች አብረዋቸው ለመሥራት ፈቃደኞች እንደሆኑ አስረድተዋል።  ታጣቂዎቹ፤ ከአራቱም ሥፍራዎች ከሌሊቱ 10 ሰዓት ለቀው ሲወጡ ወደ ሰማይ የሩምታ ተኩስ ማድረጋቸው የታወቀ ሲሆን፤ በማግስቱ ጠዋት ታጣቂዎቹ የበተኗቸው በርካታ በራሪዎች በሁሉም ቦታዎች ተገኝተው በህዝቡ ተነበዋል።

ስለ ጉዳዩ  የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራሮች በሰጡት አስተያየት  "መለብልብ ሲበዛበት፤ እንኳን ሰው ወተትም ይገነፍላል" ብለዋል። " ሰኔ 29 ቀን በሰሜን ሸዋ የታየው የታጣቂዎች እንቅስቃሴ የመለስ ዜናዊን ለከት ያጣ እብሪት ለማሰቆም በመላው ሃገሪቱ እያስገመገመ ከላው ቁጣ ካፈያው ነው የሚል እምነት አለን"ያሉት የግንቦት 7 መሪዎች፤"አፈናውና ግፉ ባፋጣኝ ሊቆም የሚችልበትን ሁኔታ በማመቻቸት ካፊያው ወደ ዶፍነተ እንዳይቀየር የማድረግ ሀላፊነት ያለው፤ አሁንም ቢሆን በሥልጣን ላይ ባለው አገዛዝ  ነው"ብለዋል።

"ይህ አይሆንም ብሎ በእብሪት ለመቀጠል ከፈለገ፣ ድርጊቱ ለሚያስከትለው መዘዝ ተጠያቂዎቹ ከአሁን በኋላ መለስ ዜናዊና ግብረ-አበሮቹ ብቻ ናቸው፡፡ በግንቦት 7 በኩል ግን፤ በሃገራችንና በዜጎቻችን ላይ የሚፈጸምን ግፍ ለማስቆም የኢትዮጵያ ህዝብ ከአሁን በኋላ በዜግነቱና በሰውነቱ ሊጎናጸፋቸው የሚገባውን መብቶች መለስን "ስጠኝ" ብሎ የሚለምንበት ምንም ምክንያት የለውም፡፡ አስገድዶ ፈልቅቆ ይወስደዋል እንጂ" በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል-የንቅናቄው፡መሪዎች።